# ሦስቱ ድመቶች - "አሳዘኑኝ" ...

ቶርባ ከማር ቤት 01/16/14

ስለመሰንበቻው ጤንነትዎ ልጠይቅዎትና ለመሆኑ ሠላም ከረሙልኝ? አማን ሰነበቱልኝ? እንዲያ ከሆነ ቆንጆ - እንኳን ለጥምቀት በዓሉ ዋዜማ በሠላም አደረሰዎት፡፡ መልካም ምኞቴ ነው፤ ልዩነቴ ከሻገተው፣ ከተንሸዋረረው፣ ከገለማውና ኋላ ከቀረው አስተሳሰብዎ እንጂ በሰብዕናዎ ዙሪያ ጣጣ የለብኝም - ክፉ አሳቢ፣ ሟርተኛ፣ ተንኮለኛ፣ ቂመኛና ምቀኛ አይደለሁምና፡፡

ስለ ሰዎች ልጆች መልካምነት፣ በጎነት፣ ስለመጻኢው ብሩህነት ሁሌም ናፋቂ ነኝና፡፡ መልካም ምኞቴን በመግለጼ መቼም እንደማያንጓጥጡኝ ተስፋ አለኝ፡፡ በተለመደው ነገር ሽንቋጭ በትርዎ እንደማይለመጥጡኝ እምነት አለኝ፣ በነገር ጅራፍዎ እንደማይርገፉኝ፣ በበትር እንደማያንቆራጥጡኝ አስባለሁኝ፡፡

ይህ ዛሬ አሮጌው ብለን የምንጠራው የፈረንጆቹ ዓመት ትናንት ባለተራ ሆኖ ሻማ ተበርቶለት፣ ርችት ተተኩሶለት፣ ኬክ ተቆርሶለትና ሻምፓኝ ተረጭቶለት በፊናው በአዲስ ዓመት ተሰይሞ ኖሯል፡፡ ዛሬ እሱ አሮጌ ሆኖ ለባለተራው ሥያሜውን ለቋል፡፡ ቁም ነገር ሊሆን የሚገባው በትናንቱ አሮጌና በዛሬው አዲሱ መካከል ያለው የመጠሪያ ልዩነት ብቻ አይደለም፡፡

ዓመት በሌላ ዓመት ይተካል፣ አንዱ ይወለዳል፤ ሌላኛው ሥፍራውን ለመጤው ይለቃል፡፡ አንዱ ይወርዳል ሌላው ይሾማል - ልክ እርስዎ አዙሪት ይመስል እየተሽከረከሩ የሊቀመንበርነቱን ሥፍራ መልሰው እንደሚረከቡት ሁሉ ይኼም አንዱ የሕይወት ዑደት መሆኑ ነውና፡፡

ለካስ እውነቴን ነውና ስንቴ ወርደው ስንቴ ተመልሰው መጡ? እኔ እንኳን ሥልጣን ናፋቂ ኢሊያም አፍቃሪ ብዬ ''ሙድ'' አልይዝብዎትም - ፈጣሪ እድሜና ጤና

ይስጠን በሊቀመንበርነቱ ሥፍራ እንደ ውኃ ቀጂ ሲመላለሱበት "ገና እናያለን ገና"፡፡ ዳሩ የዴሞክራሲያዊ የሥልጣን ሽግግር ነው ብለው እንደማያላግጡብኝ ተስፋ አደርጋለሁኝ ዶክተር መረራ ጉዲና - የተከበሩ "ሂያጅ ተመላሽ፣ ተመላላሽ ሊቀመንበር" አደራዎትን፡፡ ይህ የእርስዎ ወደ ሥልጣን መንበር ምልልስ ዘመናዊ ራስን በራስ የመተካካት ሥልትና ሥትራቴጂ ይሆን? "ድንቄም"፡፡

ሰዎች ስንባል ተስፈኞች ነን፡፡ ለነገሩ ተስፋ የሚባል ባይኖር ምን ይውጠን ነበር? ሰዎች ሁሌም በኑሮአቸው ለሕይወታቸው መሻሻል ሲሉ፣ ለኑሮአቸው መለወጥና መቀየር ይበጃል ያሏቸውን ሊከውኑ ለራሳቸው ቃል ይገባሉ፡፡ አስገዳጅ የለባቸውም - አስገዳጁ የራሳቸው ህሊና ብቻ ነው፤ ታማኝነታቸውም ቢሆን ለእሱ ነው፡፡

እንዲህ አቅጄ፣ ይኼን ከውኜ፣ ያንን ትቼ፣ ይኼን ይገቶ፣ በዚህ ለውጬ፣ ከዚያ ማዶ ወጥቼና ወርጄ ኑሮዬን እመራለሁ፣ በተሻለ ደረጃ እለወጣለሁ በሚል የየራሳቸውን ንድፍ ያወጣሉ፡፡

ኸረ ለመሆኑ! ግለሰባዊ እቅድና ክንውን ባይገጣጠም ማን ጠያቂ፣ ማንስ ተገምጋሚ ይሆን ነበር? የትኞቹ ተፈፀሙ፣ ስንቶቹስ የአፈጻፀም መሰናክል ገጥሟቸው ከመንገድ ወደቁ? ጠያቂ፣ ወቃሽና ከሳሽ የለም - ቀደም ተግባብተን የለ ከራስ ህሊና በቀር ከቶ ማን ሊጠይቅ? ለነገሩ ከህሊና በላይ ማንስ የበላይ ይገኝ ይሆን፡፡

መንግሥትም ቢሆን በፊናው ያቅዳል፡፡ የክንውን አፈጻፀሙን ይፈትሻል፡፡ ተጠያቂነት አለበትና ተግቶ ለክንውኑ ስኬት ይበጀኛል የሚለውን ጊዜ ቀምሮ፣ ዕቅድና ስትራቴጂ ነድፎ ይንቀሳቀሳል፡፡ በጤናው፣ በትምህርቱ፣ በመንገድ ግንባታውና በሌሎችም ዘርፎች እኚህን ተግባራት ከውኜ፣ የዜጎቼን ሕይወት ለውጬ፣ የሀገሬንም ዕድገት በዚህን ያህል ከፍ አድርጌ ልገኝ ብሎ ይወጥናል፡፡

የታቀደው ሰምሮ፣ ቃል የተገባው ሆኖ ሲገኝ እስክስታ ባንመታም እሰየው ነው፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣናቱ ቃልና ተግባር ገጥሟልና የሕዝብ ቅቡልነትን አግኝተው ከበትረ ሥልጣኑ ላይ ይገኛሉ፤ በሥልጣናቸውም ይቀጥላሉ፡፡ ቃልና ተግባር ለየቅል ሆኖ ከተገኘም ከሕዝብ ጋር የነበራቸው እህል ውኃ አብቅቶ እንደወጡ መውረድ

ግድ ይላቸዋል፡፡ እናም ሳይወዱ ግድ ነውና መለያየቱ አይቀርም - እየቋመጧትም ቢሆን ከሥልጣኗ ላይ መነሳት አይቀሬ ይሆናል - ለሌላ ዙር ሌላ አዲስ ዝግጅት፡፡

ገዥው ፓርቲ አሳካዋለሁ፤ በዚህም የሕዝቡን ኑሮ አሻሽልበታለሁ፣ የሀገሪቱንም ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ አሰልፍበታለሁ ብሎ የተነሳሳበትን ጉዞ ጀምሯል፡፡ ውጥኔን ዳር ሊያደርሱ ያስችሉኛል ያላቸውን እቅዶቹን ይፋ አድርጓል፡፡

ውጤቶቹ ምንም ይሁን ምን በሂደት የሚታዩ ይሆናል፡፡ ግና ጅማሮዎቹ ተስፋ ሰጪ ስለመሆናቸው ከወዲሁ አያያዙን አይቶ መፍረድ "አጉል ደፋር" ስም አያሰጥም፡፡

ፕሮግራም ቀርፆና አጀንዳ ነድፎ ሀገራዊ አቅምንና የህዝብ ተሳትፎን ተማምኖ ትላልቅ የሚባሉ ፕሮጀክቶች ተጀምረው ሂደታቸውን ጠብቀው እየተከወኑ ነው፡፡ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ከፍፃሜ እንደሚደርሱም ይታመናል፡፡ እሰየው - የእኔ ጀግና፡፡ ጥሎብኝ ጀግና እወዳለሁ፡፡ ሰነፍ አይመቸኝም፤ ሰነፍ እጠላለሁ፡፡ ማን ሰነፍ ይወዳልና?

በነገሬ ላይ ስለ ስንፍና ሲወራ ትውስ ያለኝን ወግ ብጤ ባጫውታችሁ ፈቀድሁ፤ እግረ መንገዳችንን ትንሽ ፈታ ቢያደርገን ብዬ ነው፡፡ የተነሳሁበትን ቁም ነገር ወደ ኋላ ላይ እመለስበታለሁ፡፡

ነገሩ እንዲህ ነው፡፡ ባልንጀራዬ ጨዋታ ይዋጣለታል፡፡ ጥሩ ነገር አዋቂ ነው፡፡ ያወጋኝ ስለሦስት ድመቶች ነበር፡፡ እንዲህ አለኝ፡፡ "ሦስቱ ድመቶች በእሜቴ ጓዳ ውስጥ ሆነው የልብ ልባቸውን ይጨዋወታሉ፡፡ ስለ ትናንት ምሽት ገጠመኞቻቸውም እያነሳሱ ወጋቸውን ይለጥቃሉ፡፡ ስማ! ልብ ብለህ አድምጠኝ" ሲል ማስጠንቀቂያ ይሁን ማሳሰቢያ ሰጠኝ፡፡ ጨዋታውን ለመስማት ፈልጌያለሁና የተባልኩትን ተቀበልኩ፡፡

እናም ጓደኛዬ ወጉን ቀጠለ፡፡ "ባለ ጥቁርና ነጭ መልኩ ድመት ገጠመኙን እንዲህ ሲል ጀመረ፤” አለኝ፡፡ ቀጠለናም ድመቱ "ይኸውላችሁ፤ ትናንት ማታ ጉድ ሆንኩላችሁ፡፡ በሥራ ድክም ብዬ በተኛሁበት እሜቴ በስኒ ማስቀመጫ ወተት ቀድተው ቢሰጡኝ እንዴት አባቴ አድርጌ ልጠጣ፡፡ ጉልበት ከየት ይምጣ?" አለ፡፡

እናም አሁንም ወጉን ቀጥሏል፡፡ "ጭንቅላቴን ቀና አድርጌ ወተቱን ለመቅመስ ምላሴን ማውጣት ተስኖኝ ዝልፍልፍ አልኩላችሁ፡፡ ወይ እኔና ወተት እንዲህ በቅርብ ርቀት እንተያይ? አይ አንዳንድ ቀን፤ ሲያጋጥም እንዲህ ነው፡፡ ታዲያ በሥራ በመዛሌ ጉልበት ጠፍቶ ወተቷን እንዲህች አድርጌ ሳልቀምሳት ዓይኔ ሲንከራተት አደርኩ እላችኋለሁ" ሲል ስለ አዳሩ አወጋቸው፡፡

እሜቴ "ሻሾ" እያሉ የሚጣሯት ሌላዋ ድመት በተራዋ "በጣም ትገርማለህ፤ አንተ ቀበጥ ነህ የኔ ጌታ!" ስትል ቀጠለች ፡፡ "ለመሆኑ አንተ ደከምኩ ትላለህ፤ የእኔን የማታ አዳሬን ብታዩ ምን ልትሉ ይሆን? ይገርማችኋል መቼም እንደ ማታ ያለ አዚም ዱካኩን በላዬ ላይ ጥሎና ሰውነቴን አደካክሞት አያውቅም፡፡" ስትል ወጓን ለጠቀች፡፡

እንዲህም አለች፡፡ "ትናንት እኩለ ለሊት አንዲት የአይጥ ”ፍሪዳ” ትከሻዬ ላይ ተቀምጣ ላይ ታች ስትንጎማለልብኝ አደረች፡፡ ሲላት ከትከሻዬ ወርዳ አፍንጫዬ ላይ የበቀለውን ጢሜን እየነካካች፣ ሲያሻት የላይና ታች ከንፈሮቼን እየደባበሰች ስትጫወትበት በዓይኔ ከማየት ውጪ ሌላ ምንም አማራጭ አልነበረኝም፡፡" አለች፡፡ አሁን … አሁን የሆነ ይመስል በልዩ አትኩሮት ተመለከቷት፡፡ ጨዋታውንም እንዳታቋርጥ በዓይኖቻቸው ተለማመኗት፡፡

እሷም ወጓን ቀጠለች፡፡ "ጉልበቴን እንደ ምንም አሰባስቤ፤ አፌን ከፍቼ እንዴት አድርጌ ልጉረሳት፣ ተሳነኝ፡፡ እባካችሁ አትፍረዱብኝ፤ አቃተኛ! በጥፍሬ መቧጠጥ እንኳን ሲሳነኝ፤ ምን ትሉኛላችሁ? አይጥ እንዲህ በሥራ መዛሌን አይታ ትጫወትብኝ፤ አላሳዝናችሁም? ያ መልካም አጋጣሚ ተመልሶ ይመጣ ይሆን?" እየቋመጠች አስተዛዝና በቁጭት ተናገረች፡፡

ሦስተኛው ጥቁር ድመት ከት ብሎ ሳቀባቸው፡፡ "ለመሆኑ የእናንተ የትናንት ማታ ገጠመኝና የሥራ ድካም ምን የሚያስገርም ሆኖ ነው እንዲህ የምታወሩት? አንቺ ወተት ለመቅመስ ተሳነኝ፣ አንተ አፍህ ላይ የተቀመጠ አይጥ ለመጉረስ በየት አባቴ ትላለህ፡፡ እዬዬ ሲደላ ነው አሉ እሜቴ፣ ኧረ ጉድ ነው፣ ያልተያዘ ግልግል ያውቃል አሉ!" ሲል በተረት ሸነቋቆራቸው፡፡

ሁለቱም የእሱ አመሻሽ እንዴት የተለየ ቢሆን ነው ገጠመኛቸውን እንዲህ ሊያጣጥል የተደፋፈረው፣ እናም ለማወቅ ጓጉ፡፡ ኧረ እባክህ ንገረና! ሲሉ በአንድነት ጠየቁ፡፡ እሱም እየተንጎማለለ እንዲህ ሲል አጫወታቸው፡፡

"መቼም እንደ ማታው ዓይነት ሥቃይ በህይወቴ ሙሉ ደርሶብኝም አያውቅ" ሲል የወሬ ጉጉታቸውን ጨመረ፡፡

"የእድሜዬ ሁሉ ሥቃይ ተጠራቅቅሞ ሚዛኑ ቢለካ የመጨረሻውን የጣሪያ ከፍታ በነካ" ሲልም ጨዋታውን ይበልጥ አሟሟቀ፡፡ "ለመሆኑ እናንተ ደከምን ብላችሁ ስትናገሩ ትንሽዬም እፍረት ብጤ አይሰማችሁም?" ሲል ድካማቸውን አቃለለ፡፡

"አንተዬ! የተለየ ምን ነገር ቢገጥምህ ነው እንዲህ የምታካብድ?" ሲሉም አፋጠጡት፡፡ እሱም ተናገረ፡፡ "ማታ በአንድ ጎኔ አረፍ ብዬ ትንሽ ለማሸለብ እንደሞከርኩ ለካስ የዘር ፍሬዬ ላይ ተኝቼበት ኖሬ እንዴት ሆኜ ተገላብጬ ልነሳ፣ ጨርሶ አቃተኝ፡፡ እንዲሁ ሲጠዘጥዘኝ አያድር መሰላችሁ! እንዴት አባቴ አድርጌ እግሬን ከፍሬዬ ላይ ላንሳ፣ ትንሽዬ የተሚጠጠች እንጥፍጣፊ ጉልበት ኖሮኝ አንድ እግሬን ባነሳሁና ከጥዝጣዜዬ በተገላገልኩ፡፡ አላሳዝንም፣ አልቻልኩም፣ ድክም ብሎኛላ! አትፍረዱ፣ ይፈረድባችኋል ነው የሚለው መጽሀፉ፡፡" ብሎ አለ፡፡

አሁንም ድረስ ፍሬው ላይ ተኝቶበት ከጥዝጣዜው ያልተላቀቀ እየመሰለው ሥቃዩ በርትቶ ተሰማው፡፡ ዓይኖቹን ጨፍኖ ከደናቸው፣ ህመሙም አሁን ... አሁን የሆነ

እየመሰለው አቃሰተ፡፡ አስተዛዝኖም ተመለከታቸው፡፡ በእርግጥም ሥቃዩ ተሰማቸው፡፡

"በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ ባለ ጥቁርና ነጭ መልኩ ድመት ሊጨክንበት አልቻለምና ከልብ አዘነለት፡፡ የትናንት ድካምና ውሎአቸውን መላልሰው እያነሳሱ ጓዳዋን የጓሊት ጥለዋት ወጡ፡፡ ወተት መጠጣት የተሳነው፣ አይጥ ያላገጠችባት እና የዘር ፍሬው ላይ የተኛበት – ሦስቱም ድመቶች፡፡ ስለ እውነት እልሃለሁ ከልቤ አሳዘኑኝ ሰነፎቹ ድመቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ሳስባቸው የሀገሬ ተቃዋሚ የፖለቲካ አመራሮች፡፡" ብሎኝ እርፍ ይኸው ባልንጀራዬ፡፡

እውነት ቢኖረው ነው፡፡ ሳላቅማማ ተስማማሁ፡፡ ወደ ኋላ ላይ ወደ ርዕሰ ጉዳዬ ለመመለስ በቀጠሮ መለዬቴን ልብ በሉ ውድ አንባብያን፡፡ ይኸው ቃሌን ጠብቄ ተመልሻለሁ፡፡ በቀጥታ ወደ ጉዳያችን፡፡

ለመሆኑ ድመቶቹንና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮቹን ምን አገናኛቸው፡፡ መልሱ ግልጽና አጭር ነው – ስንፍና፡፡

ይህን ጽንሰ ሃሳብ መነሻ ይዘን የኢትዮጵያ መንግሥት የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል፣ የአገሪቱንም ደረጃ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ ለማሰለፍ ያስችሉኛል ያላቸውን እቅዶች ወጥኖ ጉዞውን ጀምሯል፡፡

ከውጥኖቹ እስካሁን ምን ያህሎቹ ተተገበሩ፤ የትኞቹ ቀሩ፣ የእስካሁኑ ጉዞ ዕቅዱን ከዳርቻው ላይ ያሸጋግሩት ይሆን? እያያዙ እንዴት ነው? ዕቅዱ ተሰናክሎ ከመሃል ተደነቃቅሮ ይቀራል ወይስ ጭራሹኑ ተደነቃቅፎ ይወድቃል? እነዚህን ሁሉ ተጨባጭ ሂደቶች በጥሞና ተረጋግቶ ፈትሾ፤ ላይ ታቹን ቃኝቶ ሲያበቃ ከድምዳሜ መድረስ የአባት ነው - ያስማማናል፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ በጭፍን ተነሳስቶና በግብዝ ታውሮ መፈረጅ ግልብ ሃሳብን ይዞ መውተርተርና መቻኮል ተገቢም አይደል፡፡ የአገሬ ሰው "የጅብ ችኩል …" እንዳይሆን ያሰጋል፡፡

መድረክ የተሰኘው የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪ ዶክተር መረራ ጉዲና ሁሌም በሚሰጧቸው መገለጫዎችና አስተያየቶች የትኛውን አመክንዮ ተጠቅመው

ከድምዳሜ ላይ እንደሚደርሱ ግራ ገብት ስላለኝ ነው በጤናቸው ይሆን እያልኩ መጠየቄ፡፡ ይህችን መጣጥፍ ለውድ አንባቢዎቼ ለማቅረብ ያነሳሳኝ፡፡

ለመሆኑ መቼ ይሆን ከሻጋታው፣ ከደንቃራውና ከኋላ ቀር አመለካከታቸው ተፋትተው በሥልጡን አስተሳሰብ ላይ መሠረታቸውን ጥለው እውን በሚሆን ተስፋ ተሞልተውና አዲስ ሀሳብ ቋጥረው የሚመጡት? እንዲህ ካደረጉማ መቼም ባርኔጣ ማድረግ አልወድም እንጂ እሱን ብድግ፣ ከመቀመጫዬም ተነስቼ የክብር ሠላምታዬን ባቀረብኩላቸው በወደድኩ፡፡

ዜጎች ተለውጠው በተሻለ ጎዳና ላይ ሲረማመዱ ይታዩኛል፤ በተመረጠ መስመር ላይ ሲመላለሱ ይታሰበኛል፡፡ ተስፋና ምኞት፡፡

አሁን በዚያን ሰሞን ዶክተር መረራ እንደ ልሣን በሚገለገሉባቸው የህትመት ውጤቶች ላይ የሚሰጧቸውን ስመለከት ይደንቁኛል፡፡ "ኸረ ምን ሆነው ነው?" እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡ በምሰጠው አስተያየት ስህተትን ላለመፍጠር ስልም ደጋግሜ ሁሉ አነባለሁ፡፡

መቼም እነዚህ “ታማኝ ልሣነ አንደበትዎ” ገና ብዙ ያስነብቡናል፤ ያልተሰሙ አሉባልታ ወሬዎችንም ያስኮመኩሙናል፡፡

ዙረው … ተዟዙረው በተለመደውና በተሰለቸው አንድ ጉዳይ ላይ አጠንጥነው ያርፋሉ፡፡ በየት በኩል ይህችን ቃል ልጠቀም ብለው ፈልገው አፈላልገው እንዲህ ይሉናል፡፡ በኢትዮጵያ ተመዝግቧል የተባለው የምጣኔ ሀብት ዕድገት ቤተ መንግሥት ውስጥ ካልሆነ በቀር በሀገሪቱ የለም ነበር ያሉት፡፡

የኢትዮጵያን ዕድገት አስመልክቶ በተለያዩ ወቅቶች የበርካታ ታላላቅ የውጭ ሀገር ሰዎችን የምስክርነት ቃል ስላለመስማትዎ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ ትዕግስቱ ካለዎት እርስዎ የካዱትን፣ ሰምተው እንዳልሰሙ የሆኑበትን፣ በውስጡ እየኖሩ

እውነታውን ላለመናገር አንደበትዎ የተቆለፈበትንና ገሀድ የወጣን ሀቅ ላወጋዎ ፈቀድሁ፡፡

ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት እያስመዘገቡ ካሉ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት ብለው ነበር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ ሒላሪ ክሊንተን፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት እያራመደ ያለው ፖሊሲም ቢሆን አገሪቱ በትክክለኛው የዕድገት ጉዞ ላይ መሆኗን ያሳያል ሲሉም ሒላሪ ክሊንተን እማኝነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ዶክተር መረራ ፈቃደኛ ከሆኑ እስቲ ተጠየቁ፡፡ ከዚህ ቀደም በዚህች ቤተ መንግሥት ተቀምጠውባት፣ ሕይወትን መርተውባት፣ ጣዕምና ምሬቷን አጣጥመውባት ያውቁ ይሆን? አይፍረዱብኝ ቢጨንቀኝ ጊዜና ነው ይኼን ማለቴ፡፡

ስለ ውኃ እጥረት ሲነሳ፣ ስለ ኤሌክትሪክ ኃይል ሥርጭት መቆራረጥ ሲነገር፣ ስለ ኑሮ ውድነት ሲወሳ ሁሌም የሚታይዎትና ማነጻፀሪያም አድርገው የሚያቀርቡት ያው የተለመደውን “ቤተ መንግሥት”ን ነው፡፡

በጨዋታዎ፣ በወሬዎ፣ በንግግርዎ፣ በተረት ተረት ጋዜጣዊ መግለጫዎ፣ ምናልባትም ተኝተውም ሳይቀር ህልምዎን ማን አይቶ ማን ፈትቶልዎ እንደሆነ እንጃ እንጂ “ቤተ መንግሥት” የምትለዋ ቃል ከአንደበትዎ ትጠፋለች ማለት ቧልት ነው፡፡ ቤተ መንግሥት … ቤተ መንግሥት … እደግመዋለሁ፤ ቤተ መንግሥት ቋምጠውበታል ቤተ መንግሥት … ይገርማል እንደቋመጧት አሁንም ድረስ አሉ ቤተ መንግሥት እያሉ፡፡

ዶክተር በእጅጉ ፌዘኛ ነዎት፡፡ ሲፈልጉ በሀገሪቱ በየዓመቱ ተመዘገበ የሚባለው ሀገራዊ ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ቤተ መንግሥት ውስጥ ነው ይሉናል፡ አሉን፡፡ ደሰኮሩ፣ አወሩ፤ ነገሩን ማለት ነው? ብሩህ ተስፋን የማጣጣል፣ በጎ ጅማሮን የማኮሰስ፣ መልካም ጉዞን የማጥላላት፣ በጎ ገጽታን የማጠልሸት - ክፉ አመል፤ ክፉ ደዌ አለብዎ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን ማስተዳደር፣ በቋንቋቸው መማር፣ ባህልና ወጋቸውን ሳይሸማቀቁ ማጎልበት የቻሉባትን አገር ዛሬ በጋራ ፈጥረው በህብረት እየኖሩባት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ዜጎች ኑሯቸው የተሻሻለበት፣ አመለካከታቸውን በነጻነት መግለጽና መደራጀት የቻሉባት አገር ሆናለች፡፡ መልካም አስተዳደርን የማስፈንና የፍትህ ሥርዓቱን የማጎልበት መልካም ጅማሮዎች  የሚታዩባት አገር ለመሆንም በቅታለች ዛሬ - ኢትዮጵያ፡፡

ታዲያ ዶክተር መረራ ስለእነዚህ እውነታዎች ለመናገር ድፍረቱን ምነዋ አጡ? ሀቅ … ሀቁን ለመግለጽ አንደበትዎ ምነዋ ተያያዘ፣ ደግ … ደጉን፣ መልካም … መልካሙን በጎ በጎውን ለማሰብ አዕምሮዎ ምነዋ አልፈቀደ? በጎ ሥራዎችን ማጥላላት፤ ሸጋ ተግባራትን ማጣጣልና ጥላሸት መቀባባት ምነዋ አስፈለገዎ?

መንግሥት በጤና፣ በትምህርት፣ በመንገድ፣ በቴሌኮም፣ በሣይንስና ቴክኖሎጂ፣ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በኃይል ማመንጫ፣ በትራንስፖርት በአጠቃላይ በመሠረተ ልማት ግንባታዎችና በሌሎችም መስኮች አገሪቱን አበልጽጎ የዜጎቹን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እየጣረ ይገኛል፡፡ ምነዋ ይኼስ አልታይዎ አለሳ?

በእነዚህም ዘርፎች ቢሆን መንግሥት የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ነድፏል፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ዓመታትም በስኬት አጠናቋል፡፡ የመልካም ውጤት አመላካች ሁኔታዎችንም አይቶባቸዋል፡፡

ዶክተር መረራ ሀቁን እየጎመመዘዎትም ቢሆን ይጎነጩ ዘንድ ግብዣዬ በእኔ ይሁን፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታዋን እያጎለመሰች በዕድገት ጎዳና ላይ ትገኛለች፡፡ ሕዝቦቿም  በተሻለ የለውጥ መንገድ ላይ በመረማመድ ኑሮን ማጣጣም ይዘዋል፡፡

ይህም ብቻ አይደለም./ በዛሬይቷ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦቿና ሕዝቦቿም መብቶቻቸው ተከብሮላቸው፣ ለአገሪቱ ብልፅግና እጅ ለእጅ ተያይዘው በጋራ እየሰሩ ስለመሆናቸው ነጋሪ የሚያሻው ጉዳይ መስሎ አልተሰማኝም፡፡

ዶክተር መረራ ዳግም ይግረምዎት./ ለዘመናት በድርቅና በረሃብና፣ በጦርነትና ስደት ስሟ በክፉ ይነሳ የነበረችው ኢትዮጵያ ዛሬ በበጎ ገፅታ መጠራትን ይዛለች፡፡

የዜጎቿን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እየታተረች ትገኛለች፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በቅድሚያ ለግብርናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠቷ እንደሆነም ይነገርላታል፡፡

ዓለም ዓቀፍቨ ተቋማት እያረጋገጡት ያሉት እውነታም ይኸው ነው - የፖለቲካ ትርፍ ለመሸቀል ሲባል ሀቅን ገልብጣችሁ ተቀበሉ፤ እውነትን ሸፍናችሁ ተመልከቱ ካላሉን በስተቀር፡፡

በግሌ እርግማን አልወድም፡፡ መርገምንም ሆነ መረገምን አጥብቄ እጠላለሁ፡፡ መሬት ላይ ያለን እውነታ በአሮጌ ብርድ ልብስ ጀቡነው፤ በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት ዕድገት የለም ብለው ለሚያሟርቱት ግን ከልቤ አዝንላቸዋለሁ፡፡

ይሁንና ሟርታቸው እንዳይዝ፣ ፍላጎትና ምኞታቸው እንዳይሰምር እፀልይላቸዋለሁ - መርገምም ሆነ መረገምን እጠላለሁ ብያችሁ የለ፡፡ ክፋትን ትተው በጎ … በጎውን ምቀኝነትን ጥለው መልካሙን፣ ከተንኮል ይልቅ ቀናውን እንዲያሳስባቸው እመኝላቸዋለሁ፡፡

ወደ ኋላ መለስ ብለው ቢያስተውሉ ዜጎቿ በችጋር ተቀራምደው፣ በጤና እጦት እግርና እጆቻቸው ተሸብበው የሚኖርባት አገር ነበረች - ኢትዮጵያ፡፡

ከሁለት አሥርተ ዓመታት በፊት ጦርነት ማባሪያ አጥቶ ሀገሪቷን ቁልቁል ይደቋቁሳትና ይከረኩማት፤ ድርቅ፣ ረሀብና ስደት የዜጎቿ መጠሪያዋ እስኪመስል ዓለም ጣቱን ይጠቋቆምባትና ይዘባበትባት ነበረች - ኢትዮጵያ፡፡

ጠኔ የዜጎቿን እጅና እግሮች አስሮ፣ ቋንጃቸውን ጠፍሮ ይዞ፣ ችጋር አንገታቸውን አስደፍቶና ማንቁርታቸውን ሰንጎ አንቆ፣ ሥቃይ ወገባቸውን አጉብጦ ለዓመታት የዘለቀባት ሀገርም ነበረች - ኢትዮጵያ፡፡

ይህ ብቻም አልነበር፡፡ ስንቱ ተወርቶ፣ ስንቱ ተነግሮ ይዘለቅ ይሆን? በየአካባቢው የሕጻናት ሰቆቃ የሚደመጥበትና የጣር ድምጽ የሚሰማባት፤ ወጣቶች ተስፋቸው ተሟጥጦ በኑሮ ጣዕም ትርጉም አልባ ግራ ተጋብተው የቆዩባት፤ አረጋውያን ጧሪ አጥተው የተፈቀደላቸውን ቀሪ የሕይወት ዘመናቸውን እንዴት እንደሚገፉ ተጨንቀው የሚጠበቡባት አገር ነበረች - ኢትዮጵያ፡፡

ኅበዝ./ በዚህች የጋራ አገራችን ስንት ጉድ አይተናል፤ ስንት ሥቃይና መከራ አሳልፈናል፤ አሣራችንን እኮ በልተናል፡፡

ዶክተር መረራ እርስዎ ምን አለብዎ./ መለኪያ ጨብጠው፣ አይስክሬም እየላሱ ዓለምዎን ይቅጩ./ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለዘመናት ከጫንቃው ላይ አልወርድ ብሎት የተቸገረበትን ድህነትን ከላዩ ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል ሌትና ቀን በሥራ እየተንደፋደፈ ይገኛልና “ሙድ” ይዘው ባያላግጡ የተሻለ ይመስለኛል፡፡

እባክዎ በተጀመረው ልማታዊና ብልፅግናዊ መነሳሳት ላይ አሸዋ ለመበተን የዘረጓቸውን እጆችዎን ይሰብስቧቸው፡፡ በተጀመረው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ላይ ቀዝቃዛ ውኃ ለመቸለስ ያሰናዷቸውን የጥፋት እጆችዎችን ይመልሷቸው፡፡

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን የሚወሰነው በሕዝብ ድምጽ መሆኑን ከልብ አምነው ተቀብለው ከእጅዎ አልወርድ እያለ የተቸገሩበትን አሮጌ መዝገብ ወዲያ ያሽቀንጥሩት፡፡

በተሰለቸው ቁም ነገር አልባ ባዶ ጩኸት የተሞላውን የገረወይና ጣሳ ጥለው፤ የተጠላብዎን ለከት ያጣ የማደናገሪያና የማደናበሪያ ቀረርቶ መንፌያ ጥሩንባዎን ወርውረው ንስሃ ቢገቡ ምክሬ ይሆናል፡፡ ጤና ላጡት፣ ጤና ለራቃቸው፣ ጤና ለነሳቸው - ጤና ይሰጣቸው፡፡

በስንፍና ተሞልቶ ወተት መጠጣት የተሳነው፣ አፉን አላቅቆ አይጥ መዋጥ ያቃተው እና የዘር ፍሬው ላይ ተኝቶበት በሕመም የተሰቃየው የድመት ስብስብ በሌላ አዲስ ቀን በጥንካሬ ተሞልተው መልሰን እናገኛቸው ይሆን? ተቃዋሚ ፖለቲከኞቻችንስ ከማጥላላት ሕመም ተፈውሰው የተሻለ ጠንካራ አማራጭ ይዘው በአዲስ ጎዳና ላይ እናያቸው ይሆን?

የምርጫ ወሬ በተሰማ ቁጥር የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ ሰበባ አስባብ እየፈጠሩ ከወዲያ ወዲህ የሚንገዋለሉ፤ ከኤምባሲ ኤምባሲ ደጅ የሚጽጽጡ ሰነፍ የሀገሬ ፖለቲከኛ መሪዎች እንደ ሦስቱ ድመቶች ሁሉ አሳዘኑኝ፡፡